የሸንጎ ድምፅ

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

ልዩ እትም ታህሳስ 2008 ዓ.ም.

SPECIAL ISSUE December 2015

# ሳይቃጠል በቅጠል

በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የሕዝብ ትግልና እንቅስቃሴ ሲካሄድ ቆይቷል።ከተካሄዱት ትግሎች ውስጥ የአገርን ነጻነት በማስከበሩ ከውጭ ወራሪ ሃይሎች ጋር የተደረገ የነጻነት ትግል የሚያኮራ ውጤት ሲያመጣ በውስጥ አስተዳደር ዙሪያም ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረውን ባላባታዊ ስርዓት ለመለወጥ የተደረገ ትግል ሙሉ ለሙሉም ባይሆን መለስተኛ ድሎችን አስመዝግቦ አልፏል። ከአርባ ዓመት በፊት በተፈጠረለት አጋጣሚ ለአስራ ሰባት ዓመት በስልጣን ላይ በቆየው፣በአምባገነኑ የደርግ የገዳዮች ስርዓት ላይ ያነጣጠረ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ ለውጥ የተደረገው ህብረብሔራዊ እንቅስቃሴ ከሸፎ በውጭ ሃይሎች የታገዘ አገር አፍራሽ የሆነ ሃይማኖትንና ጎሳን(ብሔርን) ያማከለ ታጣቂ የጎሳ ስብስብ ስልጣኑን ቀምቶ እስከአሁን ለመቆየት ችሏል።ምንም እንኳን ሕብረብሔሩ ትግል በገጠመው ውስጣዊና ውጫዊ ችግር በመዳከሙ የስልጣን ዘንጉን የትግራይ ተገንጣይ ቡድን ከጥቂት አጃቢ ጎሰኛ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ቢወስድም፣ በፈለገው መንገድ አገሪቱን ለማስተዳደር አልቻለም።ከመጀመሪያው እለት ጀምሮ ሕዝቡ እምቢባይነቱን በልዩ ልዩ መልክ ሲገልጽ ቆይቷል።አሁንም እየገለጸ ነው።

ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ፈጦ የመጣው አደጋ የአገሪቱን አንድነትና የሕዝቡን ባለብዙ ትስስር ግንኙነት እያፈረሰ ለባሰ አደጋ ለመዳረግ እንደመመሪያ ዘይቤ አድርጎ የሚከተል ይኸው ጎጠኛ ስርዓት በሚያቀነቅነው መርሆ ገና ከጅምሩ አብሮ የኖረውን የሰሜኑን ኢትዮጵያ ሕዝብ

የሸንጎ ድምፅ

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

# ልዩ እትም ታህሳስ 2008 ዓ.ም.

# SPECIAL ISSUE December 2015

ኤርትራዊና የተለየህ ነህ በማለት የጣልያንና የእንግሊዞችን ብሎም የአረቦችን ፍላጎት በመተግበር ተለያይቶ እንዲኖር ብቻ ሳይሆን በቋሚ ጠላትነት እንዲተያይ ብሎም ወደአላስፈላጊ ጦርነት ከቶ የብዙ ዜጎች ሕይወት በከንቱ እንዲጠፋ ማድረጉን ባይናችን አይተናል።መሳሪያ አለኝና ያሻኝን አደርጋለሁ በሚል እብሪት ተወጥሮ ሕዝብ ፈቅዶ ያልተቀበለውን የመንግስትነት ሰሌዳ በጉልበት ለጥፎ ባሰፈነው አስተዳደር ሕዝብን ከሕዝብ ለመለያየትና አገር የማፈራረሱን ዓላማ ለማሳካት በሃይማኖት፣ በቋንቋና በክልል ከፋፍሎ ሰላም መረጋጋትና አንድነት እንዳይኖር በትጋት ሲሰራ ቆይቷል። አሁንም እየሰራ ነው።

እወክለዋለሁ የሚለውን የአገሪቱን ዜጋ የትግራይን ማህበረሰብ ከነበረበት ችግር ሳያላቅቀው በጎሳ ስሜት በማገት በሌሎች ላይ ለሚፈጽመው በደልና ግፍ መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም ቢሞክርም ያሰበው ተንኮል እየተጋለጠ በመምጣቱ በውስጡ ሽኩቻ ከተከሰተ ውሎ አድሯል።በዙሪያው ያለበትን አደጋ ለመቀልበስና የያዘውን ስልጣን ላለማጣት የሞት የሽረት ሙከራ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ካነሳሱ የዘመረውን "ቢሆን ይሆናል ባይሆን አይተነው፣እንሄዳለን አደባይተነው፡"የሚለውን መነሻ መፈክር እውን ለማድረግ አገሪቱ እንደአገር፣ሕዝቡም እንደ አንድ ሕዝብ የማይኖሩበትን አስልቶ የቀየሰውን የጥፋት ጎዳና ይበልጥ እያጠናከረው መጥቶ አሁን ወደ መጨረሻው ጠርዝ ላይ ያደረሰው ይመስላል።

በወያኔ የጎሳ ፍልስፍና የተጠመቁት ሌሎቹ ጠባብ ጎሰኞችም ከባቢያቸውን አጥረው ፣ ተገንጥሎ ለመኖር ያላሰለሰ ትግል አድርገዋል፤ በማድረግም ላይ ናቸው።

ወያኔ በነሰነሰው መርዝ ያልተበከለ ያገሪቱ ዜጋ ቢኖር በጣም ጥቂቱ ነው።አሁን ስለብሔሩ እንጂ ስለህብረብሔር፣ ስለኢትዮጵያዊነት የሚያወራውና የሚቆረቆረው ቁጥሩ እየተመናመነ መጥቷል። በኢትዮጵያዊነት ከሚሰለፈው ይልቅ በጎጥ ድንኳን ውስጥ የተሰገሰገው ይበዛል።ስለአንድነትና ዴሞክራሲ

የሚናገሩትም “ተቃዋሚ” ነን ባይ ድርጅቶች ቅድሚያና ዋጋ የሚሰጡት የድርጅት ጥንካሬአቸውንና በዚያ ለስልጣን የሚበቁበትን እንጂ ተባብረው አገር በማዳኑ ተግባር ላይ አይደለም።አንዳንዶቹም እግራቸውን በኢትዮጵያዊነትና በጎሰኝነት መሰላል ላይ አንጠልጥለው “አይተነው ጊዜ ወደሚያደላው” በሚል ስልት ወደሚያደላው ለመገልበጥ ጊዜና ሁኔታውን እየተጠባበቁ ይገኛሉ።የተቃዋሚው ጎራ ለአንድ አይነት ዓላማ ተባብሮ ከመሰለፍና ወያኔ የሚሰነዝረውን አደጋ ከመቋቋም ይልቅ ተለያይቶ እየጮሁ መጠቃትንና ማስጠቃትን ሙያ አድርገው ይዘውታል።

በሕዝቡ በኩል የሚታየው ሌላው ድክመት ከአገር አንድነት፣ከጋራ ጥቅምና መብት ይልቅ በሆነ ባልሆነው ጎጂ ተግባር ላይ ተሰልፎ የራሱን ኑሮ በማደላደሉና ለጥቅም ህሊናውን መሸጡ ነው።አገር ሳይኖር ዘላቂ ሰላማዊ ኑሮና ደስታ እንደማይኖር ቢያውቅም እለታዊ ጥቅም አስሮና አውሮ ይዞታል፤ክብርና አገሩን ለሆዱ ሸጦ ማደር እንደ አዋቂነት እየታዬ ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ጥቅም መቆም እንደ ጅልነት የተቆጠረበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።በአገሩ ተከብሮ ለመኖር የሚችልበትን መብት በጋራ ታግሎ ከማስከበር ይልቅ በውጭ አገር ተሰዶ ለመኖር እግሬ አውጭኝ ማለቱን የሚመርጠው ቁጥሩ ቀላል አይደለም። ከተሰደደም በኋላ ስለአገር ክብር፣መብትና ሰላም ዋጋ ከተሰደደበት አገር ሕዝብ አይቶ ሊማር ባለመቻሉ በድርጅት፣በሰፈርና በጎሳ ልጅነት ተሰባስቦ በጠላትነት እየተያየ ይኖራል። ኢትዮጵያ በብዙ ወጭ ያስተማረቻቸውም “ምሁራን” ለጥቅምና ለዝና እውነትን እየካዱ የሃሰት ታሪክ ምስክርነት እየሰጡ ላለውና ለሚመጣው አምባገነናዊ ስርዓት በአደባባይ ሲሰብኩና ሲደግፉ ይታያሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ለቁራሽ መሬት ሲል አሰደደኝ የሚለውን መንግስት በመደገፍና በስለላ ስራ በመርዳት በመሬት ቅርምቱ የተሳተፈው ቁጥሩ ትንሽ አይደለም።በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩት ደካማ ዜጎች ማወቅ የሚኖርባቸው ነገር ቢኖር ሕገወጥ መንግስት ሲወድቅ በሕገወጥ መንገድ የያዙትን ንብረትና ሃብት በሕግ

ሊነጠቁ እንደማይችሉ ነው።ከዚያ በላይ ግን ጥሎ የሚሄደውን ሃፍረትና የህሊና ቁስል ሊያስቡት ይገባል።ከደርግ ገዳዮች ሊማሩ በተገባ ነበር።

ወደሰሞኑ የአገራችን ሁኔታ ፊታችንን መለስ ብናደርግ ተስፋ ከሚሰጠው ይልቅ ተስፋ አስቆራጭ የሆነው ሂደት ጎልቶ ይታያል። ወያኔ በቀመረው ስሌት የሚመራው ተቃውሞ የጎሰኝነት ነጋሪት እየጎሸመ የአገሪቱን ሰላምና አንድነት በመፈታተን ላይ ይገኛል፤ዜጋ ለዘመናት ከኖረበት አካባቢ በቋንቋውና በእምነቱ ምክንያት እየተፈረጀ የሞተው ሞቶ የተረፈው ንብረቱን እየተቀማ ተፈናቅሎ በመሰደድ ላይ ነው።በምዕራብ ደቡብ፣በሰሜንና በመሃል ኢትዮጵያ እየተካረረ የመጣው ጎሰኛ ተቃውሞ ለአገሪቱ ሰላም፣ አንድነት ለሕዝብ መብትና ለፍትሕ መረጋገጥ ዋስትና የሚሰጥ ሳይሆን ጎጠኝነትን ይበልጥ የሚያናፍስና የመበታተንን አደጋ የሚጋብዝ የአጥፍቶ መጥፋት ዘመቻ ነው። በጥቅም ሸኩቻ ከወያኔ ጋር  የሚነሳ ግርግር ለሁሉም ሕዝብ የሚጠቅም ለውጥ ያመጣል ብሎ በቸልታ ማየት ወይም መደገፍ አደገኛና የዋህነት ነው።በብሄር ስም ያጠነጠነ ትግል ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ሕዝባዊ ትግሉ በወያኔ መቃብር ላይ ዴሞክራሲ ስርዓት እንዲያብብ የሚያበቃ እንጂ ሌላ ጎሰኛ ተተክቶ ለዳግመኛ ዙር ስቃይ የሚያመጣ ስርዓት እንዲመሰረት መሆን የለበትም።ጎሳና ሃይማኖት ተኮር ትግሎችና ተቃውሞዎች ብሔራዊ ይዘት የላቸውም፤ የሚቆሙት ለተነሱለት እምነትና ጎሳ ነው።ማለትም የነሱ እምነትና ጎሳ አባል ያልሆነውን በማጥፋትና ወይም በማስገደድ በራሳቸው እምነትና ጎሳ ቁጥጥር ስር ለማድረግ ነው።

ሰሞኑን በኦሮሞ ተማሪዎች በተካሄዱትና በመካሄድ ላይ ባሉት የተቃውሞ ሰልፎች በአንዳንዶቹ የተወረወሩት መፈክሮችና ያንንም ተከትሎ የተካሄዱ ተግባሮች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ በተለይም በአማራው ተወላጅ ላይ የተሰነዘረ የጠባብ ጎሰኞችን ፍላጎት የሚያጎላ ደባ እንደሆነ በጉልህ ታይቷል።ማንኛውም ሰብአዊ ና ዴሞክራቲክ አመለካከት ያለው ያንን ማጋለጥና መቃወም ይኖርበታል።ሰላምና እኩልነትን የሚሹ ሁሉ አደባባይ ወጥተው

ድምጻቸውን ማሰማት ይኖርባቸዋል። በተለይም ጉዳዩ የሚመለከተን ኢትዮጵያውያን ግፍንና ኢሰብአዊ ድርጊትን በዝምታ ልንቀበለው አይገባም። መቃወምና ፣ማጋለጥ የጋራ ስራችን ሊሆን ይገባል። የዛሬው ዝምታ ነገ አገረቢስ ለሚያደርገን ዕድል የሚያስገባ የጥፋት በር ነው። ዩጎዝላቪያን ያዩ ባገር አይቀልድም!ምናልባት በውጭ አገር በመኖራችን የትውልድ አገራችን ጥቅም ላይታየን ይችል ይሆናል፣ግን ወደድንም ጠላንም በምንኖርበት አገር እንደመጤና እንግዳ እንጂ እንደሙሉ ዜጋ የማንታይ መሆኑን መካድ የለብንም፤ ማለትም ከአገር በላይ አገር አይኖርም ማለት ነው።ከየት መጣህ ?ለምን መጣህ?መቼስ ትሄዳለህ?የሚለው ጥያቄ የማይነሳብን፣ዘረኛ ዓይኑን አፍጦ የማያይብንና እኛም አንገታችንን ደፍተን በስጋት የማንኖርበት በአገራችን መሬት ብቻ ነው። ለጊዜው በብዙ መልኩና በምቾት ያለንበት የስደት አገር ሊሻል ይችላል፣ግን ሁኔታው ሲለወጥ፣ የሕብረተሰብ አለመረጋጋትና ነውጥ ቢነሳ ቀድሞ በትሩ የሚያርፈው በእኛ ላይ ሊሆን እንደሚችል ልናስበው ይገባል። በልዩ ልዩ ምክንያቶች በተለይም ጥቂት አልጠግብ ባዮች የሚያወጡት ሕገአራዊት የዘረፋ መመሪያ ህብረተሰቡን በመበከል ሰብአዊነት እየተረሳ ዓለም በዘረኝነት ወረርሽን እየተለከፈች መምጣቷን ልንክደው የማንችለው ሀቅ ነው።ቀድሞ ከስራ የሚባረረው፣ቤት አልባ የሚሆነው የተለዩ የቆዳ ቀለም፣ቋንቋ፣እምነትና ባህል ያለው ማህበረሰብ ነው። ይህ በታሪክ ተደጋግሞ የታዬ አደጋ ነው።ካለውና ከመጭው አደጋ ለመዳን ለስደት ኑሮ የዳረገንን ምክንያት አሶግዶ የእኔ ነው በሚሉት አገር ከዘመድ አዝማድ ጋር በሚያውቁትና በሚፈልጉት ከባቢ ውስጥ መኖሩ መታደል ነው።ለዚያ ደግሞ የግድ መታገልና ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።የዜግነት መብትና ፣መልካም አስተዳደር በትግል እንጂ በጸሎትና ልመና የሚገኝ ወይም እንደመና ከሰማይ የሚወርድ የመለኮት ጸጋ አይደለም። ስለሆነም ኢትዮጵያን እንደአገር እንድትቆይና የምንሻ ዜጎች የመጣውን የመበታተን አደጋ ልንቀለብሰው ይገባናል።

ችግሩ ከሮ የሚታይባቸው ከባቢ ተወላጅ የሆኑ ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን በተለይም የትግራይ፣ የኦሮሞ፣ የደቡብና የምስራቅ ማህበረሰብ ተወላጆች እንደ ሰው የማሰብና የማሳሰብ አላፊነት አለባቸው።በነሱ ስም ኢሰብአዊና ኋላ ቀር የሆነ ጎሰኛ የፖለቲካና የእምነት መርዝ ሲረጭ በዝምታ ሊያልፉት አይገባም። ጸረ ዴሞክራሲ የሆነው የራሳቸው ጎሳና አክራሪ የሃይማኖት ተከታይ እነሱንም ሊያጠፉቸው እንደሚችል ቀድመው ሊያውቁት ይገባል። ለጥቃት ከተጋለጠውም በኩል ተመሳሳይ እርምጃ ሊሰነዘር እንደሚችል ተገንዝበ ሳይቃጠል በቅጠል እንደሚባለው ችግሩን ለማሶገድ ቢረባረቡ የተሻለ ይሆናል።በአንዱ ጉዳት ላይ ሌላው በሰላም ሊኖርና ሊጠቀም እንደማይችል መታወቅ አለበት።

ወያኔ በጫረው እሳት እሱም አገርም እየተለበለበች ነው።በወያኔ ላይ የተሰነዘረ ተቃውሞ ሁሉ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚበጅና የተሻለ ለውጥ ያመጣል ማለት አይደለምና መልካሙን ከመጥፎ እየለዩ መጥፎው እየከሰመ ጥሩው እየፈካ የሚመጣበትን መንገድ መከተል የብልህ ዜጋ ድርሻ ነው።የነበረው ድክመት፣መነካጠልና ከዳር ቆሞ መመልከት ከቀጠለ ሁሉም ከሳሪ እንጂ አትራፊ አይሆንም።አንዳንዶቹ ተቃዋሚዎችና የዜና መድረኮች የሚካሄደውን ትክክለኛውን የሕዝብ ተቃውሞ ከጎሰኛና የጥላቻ እንቅስቃሴ ጋር ያለውን ልዩነትና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ሳያጤኑ ጸረ ወያኔ ስለሆነ ብቻ በመደገፍ ያስተጋባሉ። ነውጠኞች የሚፈጽሙትን ወንጀል እንደ ጀብዱ በመቁጠር ሞቅ ሞቅ አድርገው ሲዘግቡ ይደመጣሉ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ወደ ገደል የሚከት እንቅስቃሴ በጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ሲካሄድ ማጨብጨብ አላፊነት የጎደለው ተግባር ስለሆነ አሰራራቸውን ሊያርሙ ይገባል። አንዳንዶቹ የሚቆጣጠሩትን የዜና ተቋም የገንዘብ መሰብሰቢያ ድርጅት አድረገው ከጋዜጠኛ ሙያ ጋር የተያያዘውን አላፊነት ዘንግተው ለሚከፍላቸው ድርጅት ጭፍን አገልጋዮች ሆነዋል።ጆሮውን ከፍቶ የሚያዳምጣቸውና

# ልዩ እትም ታህሳስ 2008 ዓ.ም.

# SPECIAL ISSUE December 2015

የገንዘብ ድጋፍ የሚለግሰው ቀና አሳቢ ዜጋ ስራቸውን ቆም ብሎ ሊመረምርና ሊጠይቅ ይገባዋል።እነሱን መቃወምና መጠየቅ ወያኔን መደገፍ አይደለም።አገሩን ከአደጋ ከመታደግ ግዴታ አንጻር እንደሆነ መታየት አለበት።

“ተቀምጠው የሰቀሉት ቆመው ማውረድ ይዳግታል” ወይም “ብጉር ከታገሱት(ፊት ከሰጡት) ከንታሮት ይሆናል”ነውና ሳይውል ሳያድር አገራችንን ሊበታትን የሚችለውን የወያኔን ስርዓትና ማንኛውንም ጎሰኛ እንቅስቃሴ ለመቋቋም መዘጋጀትና መተባበር ጊዜው አሁን ነው።ከዋለ ካደረ በቀላሉ ሊወገድ የሚችለው ችግር አዳጋች ይሆናል።

በተባበረ ትግል የጋራ ጠላታችንን እናሶግድ፣ ያገራችንን አንድነት እናስከብር!!

ስለ ሸንጎ ይበልጥ ለመረዳት ወይም ግንኙነት ለመፍጠር በሚከተለው አድራሻወች ሊያገኙን ይችላሉ

ድረ ገጽ Website: http://www.ethioshengo.org

ኢሜል shengo.derbiaber@gmail.com or

shengo.pr@ethioshengo.org

Tel (ስልክ) 44 793 760 0756 or ወይም

1 916 848 6790